# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር33

መስከረም 22 ቀን 2015(02-10-2022)

ካለፈው እሁድ የስርጭት ክፍለጊዜያችን ወዲህ ብዙ የታዘብናቸውና የሰማናቸው ድርጊቶች ሲኖሩ ከነዚህ መካከል ጎላ ብለው የታዩት የደመራና የመስቀል አከባበር፣በመስቀል እለት ማግስትም ህይወቱ በድንገት ስላለፈችው ታዋቂ ድምጻዊ ማዲንጎ አፈወርቅ ሃዘንና የቀብር ስነሥርዓት፣የቤተሰቡንና የሙያ ጓደኞችን ጥልቅ ሃዘን ፣የመንግሥት አካላት ሃዘኑን የፖለቲካ መሣሪያ ለማድረግ የሄዱበትን መንገድ፣ በዚያውም የአድርባይነትን ልክ የታዘብንበት ነበር።በዚሁ ቀን በወለጋ ውስጥ ከሁለት መቶ በላይ አማሮች በግፍ በኦነግ ኦሕዴድ ጥምር ሃይሎች መጨፍጨፍ ብቻም ሳይሆን፣ እንደ ደመራ በዓሉ ችቦ አስከሬናቸው ተሰብስቦ መቃጠሉ በመሪዎቹ፣ ባጃቢዎቻቸውና፣አድር ባይ ጋዜጠኞች በተጠቀጠቁበት የመገናኛ ብዙሃን ትኩረት ያላገኘ መሆኑን ብቻም ሳይሆን አዲስ አበባ እንዳይገቡ መንገድ ላይ ስለታገዱት የአማራ ተወላጆች ሌሎች ሌሎችንም አሳዛኝ ድርጊቶች የታዘብንበትና የሰማንበት ሰሞን ነበር።

ጉደኞች እዩተቀያዩሩ በሚገዙባት አገራችን የማይሰማና የማይታይ ጉድ የለም።እንደው በደፈናው የጉድ አገር ማለቱ ሳይሻል አይቀርም።ከመንግሥት ጀምሮ እስከ እምነት ተቋማቱ፣ከፖለቲካ ድርጅት ጀምሮ እስከ ሠፈር እድር፣ከሙያ ድርጅቱ ጀምሮ እስከ ግል የሥራ ዘርፍ ድረስ በሁሉም አቅጣጫ የሚከናወነው አገር ከገባችበት ማጥ ውስጥ ለማውጣት ሳይሆን ይበልጥ ሌላ አዘቅት ውስጥ በሚነክር ተግባር የሚወዳደሩባት አገር ሆናለች።የሰፈነውን ምስቅልቅል አገራዊ ችግር ለመፍታት ሳይሆን በችግሩ ጀርባ መጠቀምን በሚሹ ቡድኖችና ግለሰቦች የሴራ ገመድ ተተብትባ መዳረሻዋ የማይታወቅ አገር ሆናለች።ከአንዱ መከራ ውስጥ ተዘፍቆ እዩዩ ሲባል ከባሰ መከራ ውስጥ መስመጥ የአገራችን መታወቂያ የሕዝቧም እለታዊ ኑሮ ሆኗል።የውጭ ሃይሎች ሳይቀሩ ጎራ ለይተው ጡንቻቸውን የሚያሳዩበት የሰሜኑ ጦርነት ሁለተኛ ዓመቱን ጨርሶ ወደሦስተኛ ዓመቱ እየተንደረደረ ነው።በዚህ ሁለት እብሪተኞች ወያኔና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና በቀሰቀሱት የሥልጣን ጦርነት ብዙ ንጹሃን ኢትዮጵያውያን በተለይም የትግራይና የአማራው ልጆች እንደ ቅጠል እረግፈዋል፤አሁንም እዩረገፉ ነው።

መፍትሔ ያልተገኘለት በጎሳ ፖለቲካ የሚሽረበው በማንነት ላይ ያነጣጠረው ጥቃት ከማህበረሰብ ወደ ግለሰብ እዩተላለፈ ብዙዎች በእምነታቸውና በአስተሳሰባቸው የሚቀጠፉበት ብቸኛዋ የአፍሪካ አገር ኢትዮጵያ ሆናለች።ቀደም ሲል በነጻነት ተምሳሌነት ሁሉም አፍሪካዊ ብሎም የጥቁር ሕዝብ ብቻም ሳይሆን ነጻነቱን ተገፎ በቅኝ አገዛዝ መዳፍ ሥር የወደቁ አገሮችና ሕዝቦች የትግላቸው ምሳሌ ያደረጓት አገራችን አሁን ላይ በድንቁርና የጎሳ ንትርክና፣የእርስ በርስ እልቂት፣የርሃብ፣የስደት ተምሳሌ ሆና በማስፈራሪያነት የምትጠቀስ አገር ሆናለች።

ጨካኝ ሥርዓቶችን እያፈራረቀች የምታስተናግደው አገር ከድጡ ወደማጡ ሆነባት እንጂ የተሻለ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን አልቻለችም።ሥርዓት ስንል ለብቻው የተንጠለጠለ ታምራዊና አይነኬ መንፈሳዊ ሃይል ያለው ሳይሆን በሰዎች ተፈጥሮ፣በሰዎች የሚተገበር፣በሰዎች ድጋፍ ላይ የተንጠለጠለ ማለታችን ነው።ያለፉት ሥርዓቶች በሙሉ ባለቤት ቡድንና ተከታይ ሕዝብ ነበራቸው፤ያሁኑም እንዲሁ።ተከታዩና ደጋፊው በማወቅ ወይም ባለማወቅ፣ተገዶ ወይም ፈቅዶ ፣አምኖበት ወይም ተጭበርብሮ ሊሆን ይችላል ቢባልም ለተጠቀሱት ዝንባሌዎች ተጠያቂ ከመሆን አይድንም። ለስርዓቱ

ምስሶና ጋሻ ከሆኑት  በተቃራኒው የችግሩን መንስኤና መፍትሔ እያነሱ የሚመረምሩና ለማሳወቅ ጥረት የሚያደርጉ፣ታግሎ ለማሶገድ የጣሩና በመጣር ላይ ያሉ  ለሃቅ የቆሙ ሰዎች አልታጡም።በዬጊዜው ያለውን ሁኔታ እዬተነተኑ ለማስረዳት ሞክረዋል።ቀበኛ ስርዓቶችም በነዚህ ደፋሮች ላይ ከእሥር እስከሞት፣እንዲሁም በማስፈራራት ድምጻቸውን ለማፈንና ከሕዝብ እይታ ለማራቅ ብዙ እርምጃዎችን ወስደዋል።

ጋዜጠኛው በብዕሩ፣ዘፋኙ በእንጉርጉሮ፣ፋኖው በትጥቁ፣ምሁሩ በትችታዊ ጥናቱ፣ባለጌና ጨካኝ ስርዓቶችን ተጋፍጧል።ብዙም መስዋእት ከፍሏል፤አሁንም እዬከፈለ ይገኛል።በዘውዳዊ ሥርዓት ጊዜ አፋኝ ተቋምና ቡድን ነበር፤በወታደራዊው አምባገነን አገዛዝም እንዲሁ ሕጻናት ልጆች ሳይቀሩ በጥይት ደብድቦ አስከሬን በዬሜዳውና በወላጆች መኖሪያ ቤት ደጃፍ የሚጥሉ ጨካኞች ነበሩ፣ላለፉት 32 ዓመታት ለሰፈነውም ጎሰኛና ጸረ ኢትዮጵያ ቡድን ለዘረጋው የኢሕአዴግ/ብልጽግና ሥርዓት እንደዚያው የሚገሉ፣የሚያፍኑ፣የሚያጨበጭቡና  የሚደግፉ ተቋማትና አድርባይ ግለሰቦች  የአገሪቱን መሬት አጥለቅልቀውታል።እነዚህ ባይኖሩ ኖሮ ያለፉትና የአሁኖቹ ጸረ ሕዝብ ሥርዓቶች አንድም ቀን ባላደሩ ነበር።

ለመሆኑ ያለፉትንና የአሁኑን ሥርዓቶች የሚደግፈውን ዜጋ  አይምሮ ምን ሰለበው ብለን ስንጠይቅ የሚከተሉትን ዋና ዋና ምክንያቶችን እናገኛለን። የጥቅም፣ የፍርሃት፣ የበታችነትና ምቀኝነት የወለደው ጎሰኝነት ሆኖ እናገኘዋለን።

በነዚህ ጥምር ድክመቶች የተነሳ አገርና አገር ወዳዶች  ለመከራ ተዳርገዋል።አሁንም በዬእስር ቤቱ ይማቅቃሉ፤የተገደሉም ብዙ ናቸው።እነዚህ ከራሳቸው በላይ ላገራቸውና ለሕዝባቸው መብትና ነጻነት የሚቆረቆሩ አገር ወዳዶች ለራሳቸው ኑሮ ቢያስቡና ቢጨነቁ ኖሮ ከማንኛውም ያላነሰ ሲሆን የተሻለ ኑሮ ለመኖር የሚያስችል ችሎታና ብቃት ያላቸው ናቸው።

ፈሪነትና አድር ባይነት ለደካሞች ዕውቀትና የማምለጫ ዘዴ ቢመስልም የማይቀረው ሕዝባዊ ፍርድ እስኪመጣ ድረስ ጊዜያዊ ምሽግ ነው።ጥቅመኝነትም እንዲሁ ለጊዜው ደስታ ቢሰጥም የኋላኋላ የሚያፍሩበትና የሚጠዬቁበት ይሆናል።ከሥርዓቱ ጋር በመጠጋጋት  ያገኙት ሃብትና ሥልጣን አብሮ አያመሽም።ሥርዓቱ ሲንኮታኮት አብሮ ይንኮታኮታል፤እንደ ሥርዓቱ ቁንጮዎች አጋርና ደጋፊዎችም በሰሩት የሚጠዬቁበት ጊዜ መምጣቱ አይቀርም።

ምቀኝነትና የበታችነት የሚነዳው ማህበረሰብ ወይም ቡድን ከዚህ ደዌ የሚያድነው ነገር ቢኖር፣ ሁላችንም የአንድ አገር ልጆች ነን፣በማንነታችን የሚከፋፍሉን የወያኔና የኦነግ፣ኦሕዴድ ብልጽግና ሰይጣናዊ አስተሳሰብ ያላቸው እራስ ወዳዶችና ጸረ አንድነት የሆኑ ቡድኖች ናቸው በማለት  ከትከሻው ላይ ለማውረድ ሰልፉን አስተካክሎ  ከሌላው ጋር  በእኩልነት ለመኖር ከቆረጠ፣ ከገባበት የጎሳና የበታችነት ጉድጓድ ፈንቅሎ ሊወጣ ከቻለ ያን ጊዜ ዘለቄታዊ ሰላምና የህሊና ደስታ ያገኛል።

ባለፉት ስርዓቶች የትኛውም ጎሳ ተወላጅ ለብቻው የደላው ኑሮ አልኖረም።ከዬጎሳው የተውጣጡ ጥቂት እራስ ወዳዶች በጋራ የተጠቀሙባቸው ሥርዓቶች ነበሩ፤ ያሁኑም ሥርዓት በባሰ መልኩ እንዲሁ።አንዱ በመደብ ሌላው በጎሳ ስም እዬተነሳ አገርና ሕዝብ ሲያምስ ኖሯል፤ያለፉት ሥርዓቶች አወዳደቃቸው አላማረም።በሕዝቡ እምቢባይነትና ትግል ተንኮታኩተዋል።አሁንም እያመሰ ያለውን ሥርዓት እስከወዲያኛው ለማሶገድ የሚቻለው ሕዝቡ ወደ ቀልቡ ተመልሶ በአንድነት ሲቆም ብቻ ነው።አንዱ የሌላው ስቃይና መከራ ሳይሰማው በራሱ ላይ እስኪደርስ ድረስ ቆሞ ከጠበቀ፣ ነገ ብቻውን ድረሱልኝ ተጠቃሁ ብሎ ቢጮህ ሰሚና ደራሽ አያገኝም፤ምክንያቱም ቀደም ሲል ሌሎቹ ተጠቅተውና ተዳክመው እንዲገኙ የድርሻውን አበርክቶ መጨረሻው ላይ እራሱን አጋልጦ ብቻውን ቆሟልና ነው።

ለሕዝቡ መብት፣ ለአገር አንድነትና ህልውና የሚታገሉት በዬእስር ቤቱ ሲሰቃዩ ሌላው ምንም እንዳላዬና እንዳልሰማ በዬጭፈራ ቤቱ አልኮል እዬተራጨ ሲውረገረግ፣ብዙሃኑ የሚልሰው የሚቀምሰው አጥቶ የስቃይ ድምጽ በሚያሰማበት ከተማ በዬመዝናኛ መድረኩ ብር እዬረጨ በኩራት ኮረዳ ለማማለል የሚራኮተው ወጣትና ጎልማሳ ለሥርዓቱ የሽፋን ካባ በመሆን ያገለገለ ስለሆነ ከታሪክ ወቀሳም ሆነ ሕዝባዊ ቅጣት የሚያመልጥ አይሆንም። ያ ከመድረሱ በፊት ሰልፉን ቢያስተካክል የተሻለ ነው።የአስረሽ ምችው ውጤቱ ምን እንደሚሆን የባቢሎን ከተማን ውድቀት ታሪክ መለስ ብሎ እንዲያነበው እንመክራለን።የአሥረሽ ምችውና የማን አለብኝ የእብሪት ሥራ መጨረሻው አያምርም። ሌላው ቢቀር አወዳደቃችሁ እንደማይቀር ተረድታችሁ ለአወዳደቃችሁ ቦታ ፈልጉለት ለማለት እንወዳለን።

ከሃይማኖት ምሁራን በኩል የሚሰጠው ትንታኔ እንዲህ ይላል

ሰይጣን ንጹሃንን የፊት ለፊት በሩ በሆነው በመንግሥት በኩል ያጠቃል።በኋላ በሩም ደካሞች በጨምላቃና በአስነዋሪ ባህልና ስነምግባራት ውስጥ፣በክህደት፣በራስ ወዳድነት፣ በአልኮል፣ በግብረሰዶምና ተመሳሳይ እንግዳ የፍትወት ባህል እንዲዘፈቁ ያደርጋቸዋል።ሆኖም ግን ሰይጣንና ሠራዊቶቹ በመጨረሻው ጊዜ የሚደርስባቸውን የፈጣሪ ቅጣት የሚቋቋሙት አይሆንም፤ያም ቀን ደርሷል በማለት ያስጠነቅቃሉ።እኛም ሞት ቢዘገይ የቀረ ይመስላል ብለን፣መውደቃችሁም ቢዘገይ እንደማይቀር አስቡት እንላለን።

ዋልጌ የኪነት ባለሙያዎችም ሆኑ የመዝናኛ መድረክ አዘጋጆች ያገራቸውና የወገናቸው ብሶት የማይሰማቸው ከሆኑና በያዙት ከበር ቻቻ ከቀጠሉበት ከሥርዓቱ ተነጥለው አይታዩም።የያዙትን የሙያ ችሎታና የመድረክ ዕድል ገንዘብና ዝና ከመሰብሰቢያነት ይልቅ ሕዝቡን በማንቃትና በመቀስቀስ፣ ወጣቱን ትውልድ በመምከርና በስነምግባር በማነጽ ሥራ ላይ ቢጠቀሙበት፣የሕዝብ ድምጽ በመሆን የአርበኝነት ግዴታቸውን ቢወጡበት ለህይወታቸውና ለታሪካቸው ይጠቅማቸው ነበር።ጸሓፊው የአቤ ጎበኛን፣የአዲስ አለማዬሁን፣የጸጋዬ ገ/መድህንን፣የበአሉ ግርማን፣የመስከረም አበራንና የሌሎቹንም ፋና መከተል ይኖርበታል።ጋዜጠኛውም የተመስገን ደሳለኝን፣የመአዛ ሞሃመድን፣የታዴዎስ ታንቱን፣የጎበዜ ሲሳይን፣አሳዬ ደርቤ፣አባይ ወልዱና የሌሎቹን ፣ሃቅና ድፍረት ማንጸባረቅ ይገባዋል።እነሱ ከሌላው የሳሳ እንጀራ አይበሉም፣እነሱ የሚረኩት በእህልና ውሃ ብቻ ሳይሆን ሃቅ በተባለ የመንፈስ ምግብ ነው። ለነሱ ቀለባቸው እውነትና እውነት ብቻ ነው።ሌሎቹ እንደነሱ ችሎታና ሙያቸውን ለአገር ህልውናና ለሕዝብ ደህንነትና መብት ማስከበር ላይ ካዋሉት ለማያፍሩበትና ለማይሸማቀቁበት ፣ ይበልጥ ተከብረውና ተወደው ለሚዝናኑበት ኑሮ ፣የትልቅና ነጻ አገር ባለቤትም ለመሆን ያበቃቸዋል። በዚህ ደረጃ የተሰለፉ ጥቂቶች ቢሆኑም መኖራቸው አይካድም። ለነሱ ትልቅ ክብርና ምስጋናም ማድረግና እንዲቀጥሉበት ማበረታታት ተገቢ ነው።በነሱም ላይ ሥርዓቱ ቢላዎ እዬሳለ መሆኑ በግልጽ ታይቷል። ሲጠቁና ሲገደሉ ደረት መድቃትና ማልቀስ ሳይሆን እንዳይነኩ ለመከላከል በሚያበቃ ቁመና ላይ መገኘት አስፈላጊ ነው።ስንቶቹ ተቀጠፉ?ስንቶቹስ እስኪቀጠፉ ድረስ ይጠበቃል? አሁን መፍትሔ የሚፈለግበት የመጨረሻው ሰዓት ላይ ተደርሷል።መፍትሔውም ያለውን ቀበኛ የጎሰኞች ስርዓት ማሶገድ ነው።ለዚያ ሁሉም አገር ወዳድ እጅ ለእጅ ተያይዞ በአንድ ላይ ጎራውን ለይቶ መታገል አለበት።

በአገራችን ለመቁጠር የሚያዳግቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ከማለት ይልቅ ሱቅ በደረቴዎች ማለቱ ሳይሻል አይቀርም፣ከችግሩ በላይ የሆኑ የእርዳታ ተቋማት ይገኙባታል።ሆኖም ግን ችግሮቹ ሲቀፈቀፉ እንጂ ሲመክኑ አይታይም።የፖለቲካ ድርጅቶቹ የአገራችንን ችግር በሚያሶግደውና መፍትሔ በሚሰጠው ቁም ነገር ላይ ከማሰብና ከመጨነቅ ይልቅ የስልጣኑ ባለቤትና ተቋዳሽ በሚሆኑበት ዙሪያ ላይ ተዘፍቀዋል።

ሌላው ቀርቶ የተቋቋሙበትን ዓላማ የመግለጽና የማሳወቅ ችሎታና ፍላጎት አይታይባቸውም።ዓላማ አለን ቢሉም ለዓላማቸው በጽናት አልቆሙም።የገቡት ቃል ኪዳን ቀለሙ ሳይደርቅ እንታገለዋለን ከሚሉት ጋር ተለጥፈው የሥርዓቱ አዛዥና ናዛዥ ሆነዋል። ፖለቲካውን ሽቀጥ፣ድርጅቱንም የሚነግዱበት ሱቅ በደረቴ አድርገውታል የምንለውም ለዚያ ነው።

የኤኮኖሚ ልሂቃኑ ለአገሪቱና ለሕዝቡ ቋሚ ካንሰር የሆነውን እርሃብና ቸነፈር ለማጥፋት በሚያስችለው ፣በአገሪቱ የጀርባ አጥንትና የብዙሃኑ መተዳደሪያ ሙያ በሆነው በእርሻው ዘርፍ ላይ ጥናትና ምርምር ከማድረግ ይልቅ በከተማ የፎቅና መዝናኛ መስክ ላይ ትኩረት ሰጥተው፣እነሱም የዚያ ተጠቃሚ ለመሆን ሲራኮቱ ይታያል።ሆቴልና የመዝናኛ ዘርፎች በቀላሉ የገንዘብ ማግበስበሻዎች ስለሆኑ ሁሉም በዚያ ላይ ይረባረባል።ከትራክተር ይልቅ በውድና ዘመናዊ መኪናዎች ያገር ገንዘብ ሲባክን በአድናቆት ያያሉ። ባለሥልጣኖችና ተባባሪዎቻቸው በዘረፉት ገንዘብ የባንክ ባለቤቶች እዩሆኑ በወለድ ላይ ወለድ እዩሰበሰቡ ሕዝቡን ሲመዘብሩ የአገሪቱንም ካዝና ባዶ አድርገውታል።የአገሪቱ ገንዘብ በነሱ ፍላጎትና ውሳኔና ተመን በጥቁር ገበያ እንዲሽከረከር አድርገው ብሔራዊ ኤኮኖሚውን አላሽቀውታል። ባዶ እጁን ሥልጣን ላይ የተቀመጠ ዘራፊ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሚሊዮን ሳይሆን የቢሊዮን ብር ባለቤት ሆኗል።ባንክም የሚያቋቁመው ይኸው ዘራፊ ቡድን ነው።ብዙሃኑ የገጠሩ ኑዋሪ ዓለም ስትፈጠር በነበረው ከባቢያዊ መልክ በጨለማና በአባጣ ጎባጣ መሬት ላይ ኑሮውን ከመግፋት አልተላቀቀም።ዘመኑ የሚፈቅደውን ንጹህ ውሃ፣የመጓጓዣ መስመር፣የኤሌክትሪክና የሕክምና አገልግሎት፣የትምህርት ዕድል ከሚያገኘው የማያገኘው ይበልጣል።ለብዙሃኑ የዓመታት ለውጥ እንጂ የኑሮ ለውጥ ሳይመጣለት ዕድሜውን በመከራና ስቃይ ይፈጃል።ሥልጣን ላይ የሚወጣው ግን በዚህ ባልታደለና ባልተለወጠ የተፈጥሮ ሸክም በተቆራኘ ሕዝብ ስም ነው።ተምሬያለሁ የሚለው ይህንን ሕዝብ ከመርዳት ይልቅ ዘራፊና ጎሰኛ የሆነውን መንግሥት ለማማከር ሲራኮት ይታያል።

ትግሉ እነዚህን ግዙፍ ችግሮች ለማሶገድና ለመፍታት እንጂ መንግሥትን ለማሶገድ ብቻ መሆን የለበትም።አዎ ለችግሩ ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መወገድ አለበት፤ግን በዚያ ሊቆም አይገባም።አንድ አምባገነን ሥርዓት ወርዶ ሌላ አምባገነን ሥርዓት ቢመጣ ችግሩ ሳይሆን የሚቀዩረው የችግሩ ባለቤት ነው። አንድ ጎሰኛ ቡድን ወር lla ጎሰኛ ቡድን ቢተካ ያው በገሌ ነው። አገራችን ለተደጋጋሚ አምባ ገነን አገዛዞች ለምን ተጋለጠች?እርሃብና ቸነፈር ለምን በተደጋጋሚ ይከሰታል?መፍትሔውስ ምንድን ነው? የአገራችን የተፈጥሮ ሃብትና አቅሟ ምን ይመስላል?ለሕዝቧ በቂ ነወይ?ምን አይነት የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበረሰብ ፍልስፍና ዘለቄታዊ መፍትሔ ይሰጣል?የለውጡ ቅደም ተከተል ምን መሆን አለበት?የሕዝቡ አብሮ የመኖር እሴቶች ምንድን ነበሩ?አሁንስ በጎሳ ማንነት ለመለያዬቱ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?የኢትዮጵያ አገራዊ ምሥረታ ከሌሎቹ አገሮች አገራዊ አመሠራረቶች በምን ይመሳሰላል፤በምንስ ይለያያል? መልካምና ጎጂ ገጾቹ ምን ይመስላሉ?ይዘናቸውና ጥለናቸው የምንጓዘው እሴቶቻችን የትኞቹ ናቸው?ለነዚህ ትኩረት በመስጠት መልስ ለማግኘትና በተግባር ለመግለጽ የሚያስችል ቁመና ላይ መገኘት ካልተቻለ ለውጥ የሰማይ ያህል እርቆ የሚመኙት ህልም ሆኖ ይቀራል።ለቀጣይ ጎሰኛና ጨካኝ ቡድንም ይዳርጋል።

በመጨረሻው ልናነሳ የምንወደው ከጀሯችን የማይጠፋውን የሞት ዜና ነው።በአጭር ጊዜ በሽታ ወይም ድንገተኛ አደጋ የብዙ ኢትዮጵያውያን ህይወት መቀጠፉ የተለመደ ሆኗል።ለዚህ የኑሮ ዘይቤና የሕክምና አገልግሎቱ ብቃት ቢስ መሆንና መዳከም በዋናነት ቢጠቀስም በዜጎች ስነልቦና ላይ የሚደርሰው ተስፋ መቁረጥና ብስጭት፣እረፍት ማጣት ለአካል መዳከምና ብሎም ለህልፈት እንደሚዳርግ የጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ።በእጅ አዙር ደባና ጥቃትም ህይወታቸውን የሚያጡት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም።በሰሞኑ የድምጻዊ ማዲንጎ አሟሟት በኢትዮጵያ በተለይም በአዲስ አበባ

ነዋሪ ልብ ላይ ጥሎት የሄደው ሃዘን ቀላል አይደለም።ስለወጣቱ ድምጻዊ ማዴንጎ አፈወርቅ ህልፈት በመንግሥት ሳይቀር የተለያዩ ውዥንብር የፈጠሩ መረጃዎች ሲናፈሱ ታዝበናል። ማዴንጎ ባደረበት ህመም የተነሳ መተንፈስ አቅቶት ፣የኦክስጅን እርዳታ ባለማግኘቱ መሞቱ ቢረጋገጥም፣በተጨማሪ ጊዜው ያለፈበት መድሃኒት መሰጠቱም አንዱ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።በመንግሥት አሻጥር እንደተገደለም ይወራል። በሕክምና ስም የተቋቋሙት የንግድ ድርጅቶች የኦክስጅን አቅርቦትን የመሰለ አነስተኛ አገልግሎት የማይሰጡ ግን ከካርድ ጀምሮ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ከመስኩ ቢታገዱ የተሻለ ነው። በዚህም ሆነ በዚያ ግን ጎልማሳው ድምጻዊ ማዴንጎ ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ህይወቱ በማለፉ የተሰማንን ሃዘን እዩገለጽን ለቤተሰቡና ለወዳጅ ጓደኞቹ ፣ለአድናቂዎቹ በሙሉ መጽናናትን እንመኛለን፤ ነፍሱንም ፈጣሪ ይማር እንላለን።የወጣቱን ሞት በሰማንበት ዕለት በሥርዓቱ የተከናወነ የግድያ ሴራ ለመስማትም ችለናል። በዚሁ በማዴንጎ ሃዘን ላይ የተቀመጠ የሙያ ጓደኛው ዳኜ ዋለ የተባለው ድምጻዊ በምሽት ወደ ቤቱ ሲሄድ በጉዞ ላይ እያለ በመንግሥት በተላኩ አፋኝና ገዳይ ቡድኖች የተፈጸመው የግድያ ሙከራ የሥርዓቱን ጭካኔና መበስበስ የሚያሳይ ነው።ሞተ ብለው ጥለውት የሄዱት ድምጻዊ በሰዎች ከወደቀበት ተነስቶ በሃኪም እርዳታ ነፍሱ ልትተርፍ ችላለች።ስለአማራ የሚዘፍን፣የሚጽፍ፣የሚናገር የሚታገል ሁሉ የሥርዓቱ አንደኛ ጠላት ተደርጎ እንዲጠፋ ተፈርዶበታል። ይህንን ሃቅ መቀበል የማይችል ቢኖር የስርዓቱ ደጋፊና ለጥቅም የተገዛ ከሃዲ ብቻ ነው።

ድምጻዊ ማዴንጎን ለመሸኘት በተዘጋጀው የስንብት መርሃ ግብር ላይ የታዩውም የሥርዓቱ ባለቤቶች የወጣቱን ህልፈት የፖለቲካቸው ካባ አድርገው ለመጠቀም የሄዱበት መንገድ እጅግ ያጋለጣቸው ሆኖ አልፏል።የወጣቱን ያገር ፍቅር ተልእኮ የነሱ አድርገው ለመንጠቅና የነሱ ደጋፊና ተባባሪ ካድሬ እንደነበር የገለጹበት መንገድ የሚያሳፍር ነው። ለማዴንጎና ለቤተሰቡም ክብር መንሳት ነው።ለቅሶዩን ቀሙኝ ብላ እንዳለችው ቤተሰቦቹን ሃዘንና ለቅሷቸውን ብቻ ሳይሆን ስብእናቸውንም የመንጠቅ ሙከራ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የታዘብነው የአድር ባይነት ገጽ ደግሞ የስንብት መድረኩን ሲመራ የነበረው ሰው፣ሰው ከተባለ!ለእኛ ግን ከሰው ደረጃ የወረደ ብቻ ሳይሆን ከውሻ በታች የሆነ አድርባይ ብለነዋል፣ አዳነች አቤቤ የተባለችውን ጨካኝና ጸረ ኢትዮጵያ/ጸረ አማራ የሆነች ፣የከተማውን መሬትና ድሆች ያሠሩትን መኖሪያ ቤት እዩነጠቀች ከመቸብቸብና ለጎሳ መሰሎቿ ከማከፋፈልም በላይ አማሮች አዲስ አበባ እንዳይገቡ ብላ መንገድ ላይ ፖሊስ አቁማ የከለከለች ወንጀለኛን በስንብቱ መድረክ ላይ ወጥታ እንድትናገር ሲጋብዝ ያደረገው የማስተዋወቂያ ንግግር እስከወዲያኛው ድረስ ተሸክሞት የሚኖረውን ሃፍረት የገበዩበት፣እኛም አድርባይነት እንዲህ በአደባባይ ገጦ ያዩንበት አጋጣሚ ነበር። ስሙን ለመግለጽ እውቅና ስለሚመስለን ባሳዩው ባህሪ ግን ስሙን ወረደ ብለነዋል።እውነትም ወረደ! ስለአዳነች አቤቤ ያለውን ለመጥቀስ ያህል ከንቲባነቷን ከገለጸ በኋላ ጀግናዋ!ቆራጧ!እያለ የማያስፈልግ ሙከሻ ማንጋጋቱ ለመጣችበት ሃዘን ቦታ የሚመጥንና የሚጠበቅ አልነበረም።የመድረክ መሪው አቶ ወረደ ግን የማዴንጎን የስንብት መድረክ የሚፈልገውን እንጀራ ለመጋገር የተጠቀመበት ምጣድ ወይም ለሚፈልገው የከተማ ቦታ ሽልማት እጅ መንሻ ጉቦ አድርጎ የተጠቀመበት ሆኖ አገኝተነዋል። የአዲስ አበባን ከተማ ነዋሪ ቁም ስቃይ ማሳዩቷ፣ አዲስ አበባ የኦሮሞ ከተማ ፊንፊኔ እንጂ የኢትዮጵያ ከተማ አይደለችም ማለቷ፣አማራ እንዳይገባ ማገዷ፣በዩትምህርት ቤቱ የኦነግን ባንዲራ እንዲሰቀል መዝሙሩም እንዲዘመር ማስገደዷ፣የእቴጌ ጣይቱ ብጡል ሃውልት በቆረቆረችው ከተማ አይቆምም ማለቷ፣ሌላውም ድፍረቷ ለዚህ አድርባይ የጀግንነት ሙያ ነው።

ሌላው ቢቀር በደመራ ቀን ይህችው ጉደኛ በመስቀል አደባባይ ንግግር ስታደርግ ይሰማ የነበረውን የሕዝብ ተቃውሞና የድምጽ እረብሻ ከግምት ቢያስገባ ኖሮ ለዚህ ቅሌት ባልበቃም ነበር።ግን አድርባይነት የህሊና ሰሌዳን ስለሚሸፍን ያ ትዝ አላለውም ወይም ክዶታል። ለሱ ትልቁ ነገር አጋጣሚውን መጠቀምና ከአዳነች አቤቤ ጋር መቀራረቡ ነው።

ችግር ሲለመድ ቤተሰብ ይሆናል እንደሚባለው የአማራው መጨፍጨፍ በዬቀኑ ሲፈጸም ሌላውን ቀርቶ አማራውን ሊቀሰቅሰው አልቻለም።የተለመደ ወሬ አድርጎታል።ከዚህ መከራ ያድነናል የተባለው ፋኖም በሽዎች እዬተነዳ እስርቤት ውስጥ ይታጎራል።የታሠረው ቁጥሩ ከሁለት ክፍለጦር አያንስም።ይህ ማለት በንጉሥ ሃይለሥላሴ ዘመን የነበረውን ያገሪቱን የመከላከያ ሃይል ግማሹን ለማከል ጥቂት የቀረው ነው ማለት ነው።አልሸባብ ከሁለት ሽህ አይበልጥም፤ግን አንድ ብቻ ሳይሆን የምስራቅ አፍሪካን አገራት እያመሰ ነው።የኦነግም ሃይል ሲጀመር ከሁለት ሽህ አይበልጥም ነበር ።አሁን ላይ ግን ስልጣን ላይ ባለው በብልጽግና ድጋፍ የኦሮሚያ መከላከያ ሃይል ለመሆን በቅቷል። በኢትዮጵያ ሕዝብ መንፈስ የተቋቋመው ፋኖ ለምን ለዚህ አልበቃም የሚለው መልስ የሚሻ ጥያቄያችን ነው።አንዱ ምክንያት ግን በባአዴን የተገዙ ቅጥረኞች በፋኖ ስም ደሃውን ገበሬ እያስገደዱ በሬና ሙክቱን እያረዱበት፤ገንዘቡን እዬነጠቁና፣እዬደበደቡ ለፋኖ የነበረውን ፍቅር በጥላቻ እንዲለውጠው እምነት እንዲያጣ አድርገታል የሚለው መረጃ ከከባቢው ታዛቢዎች በኩል ይቀርባል። እውነተኛው ፋኖ ለስሙና ለዓላማው ሲል በስሙ ግፍ የሚሠሩትን ለይቶ በሕዝቡ ፊት ቅጣታቸውን መስጠት ይኖርበታል።ለሌሎቹም መቀጣጫ ይሆናል።በዋናነት ግን ላኪውን ባአዴንን መቅጣት የችግሩን ምንጭ ማድረቅ ነው።ከሁሉም በላይ ግን በተደጋጋሚ እንዳልነው የተበታተነው የፋኖ ሃይል በአንድ ድርጅታዊ መዋቅር ሥር መሰለፍ አለበት።የፖለቲካና የትጥቅ ትግሉ በመርሃግብር መመራት አለበት።ሌላው ቢቀር ከኗላ ቀሩ ኦነግና ህወሃት ሊማር ይገባዋል።እነዚህ አገር አጥፊዎች ለቆሙለት የጥፋት ዓላማ የሚመራቸው ማእከላዊ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራር አላቸው።ለዚያም ነው ወድቀው የማይወድቁት።እነሱን ለማሸነፍ ከነሱ በላይ ድርጅታዊ አቅምና በሳል አመራር ያስፈልጋል።

የኦነግ መራሹ ብልጽግና የድፍረቱ ድፍረት አሁንም ከአማራው ክልል የሚመጡትን መንገደኞች አግዶ በአውቶቡስ ውስጥ ወሎዬዎች እንዳሉ እዬጠዬቀ ሌሎቹን በጅራፍ እዬገረፈ ወደመጡበት መመለሱን ችግሩን የተቀበሉት ይፋ አድርገዋል።የውጭ አገር ፓስፖርትና የአዲስ አበባ የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው ሳይቀሩ የዚህ ዘረኛ ድፍረት ሰለባዎች ሆነዋል።ዘመድ ለመጠዬቅ ከቤታቸው እንደወጡ ሜዳ ላይ እንዲፈሱ ተደርጓል።የዚህን ድርጊት በቦታው የነበሩና የችግሩ ተካፋይ የሆኑት አንዱ አቶ ገለታው ዘለቀ በላኩት የጽሑፍ ማስረጃቸው አረጋግጠዋል።

ወሎዬዎቹ ለምን ተለይተው ተጠዬቁ ለሚለው ፣ወሎ ኦሮሞ ነው የሚል አቋም ስላላቸው ከዚያ የሚመጣውን በዚያ ህሳቤ ለማጥመቅና ቤተሰቦቹን መያዣ በማድረግ በአሸባሪ ተግባራቸው እንዲሳተፍ ለማድረግ ይሆናል የሚል ግምት አድሮብናል።አማራ መሆኑም ከተረጋገጠ በመግደል ቁጥሩን ለማመንመን ነው የሚለው ተጨማሪ ግምታችን ነው።በተመሳሳይ ብአዴን የተባለው የኦነግ ኦሕዴድ ታማኝ አሽከር አማራው በራሱ ከተማ በባሕርዳር እንዳይገባ ተመሳሳይ እገዳ ጥሎበታል።ይህ ከንቱ ባንዳ ድርጅት በአማራው ስም ስልጣን ቢይዝም ለአማራው መብት አልቆመም።በኦነግ ሲጨፈጨፍ፣ ሲፈናቀልና አሁንም አዲስ አበባ አትገባም ተብሎ ሲንገላታ ለምን ብሎ አልጠዬቀም፤ይባስ ብሎ ታማኝነቱን በተመሳሳይ መንገድ ገልጿል።በአማራው ተወላጅ ላይ ይህንን የመሰለ ግፍና በደል የሚፈጽመው የተረኛው ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና በአዲስ አበባ በኦሮሞ ስም ለማክበር ባዘጋጀው እሬቻ ለተባለው የጣኦት በዓል ብዙ ሚሊዮን ብር ወጭ ያደረገ ሲሆን ለበዓሉ ለሚመጡትም ሰዎች ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎት መድቧል።ይህን የመሰለ እብሪተኛና ተረኝነት በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም።

እሬቻ በወንዞች ዳርቻ የደም ግብር እዬቀረበ ፣ፍጹም ኋላቀርና ሰይጣናዊ መንፈስ በሆነ የዛር ጭፈራ የሚከናወን፣ ዛፍና ቋጥኝ ቅቤ እዬተቀባ የሚመለክበት ጣኦት ለመሆኑ ማንም አይክደውም፤ሌላው ቢቀር በህይወት ያሉ በተለይም በገናሌና በደብረዘይት ሆራ ወንዞች አካባቢ የሚኖሩ ይመሰክራሉ።

ሃቀኛ ኦሮሞዎችም ይናገራሉ።በብዙ የውጭና ያገር ውስጥ ጸሐፊዎች በጸፉት ታሪክም ተመዝግቧል። በስማ በለው እንደሚነገረውማ ከሆነ ከአስር ዓመት ዕድሜ በታች የሆነ ልጅ ለወንዙ ጭዳ ይደረግ ነበር ይባላል።ያንንም ተከትሎ ሳይሆን አይቀርም የሆራው ቆሪጥ የልጅ ግብር ለምዷል እዬተባለ በልማድ የሚነገረው።ይህ እውነት ከሆነ ኦሮሞውን ብቻ ሳይሆን መላውን ኢትዮጵያዊ ብሎም አፍሪካዊ የሚያሳፍር ድርጊት ነው።የምዕራብ አፍሪካን የፉዱ ጣኦት ስንመለከትና የሰው ልጅ ሰውነት ተቦጫጭቆ ልቡና ኩላሊቱ ሳምባው ሳይቀር ሲበላና ግብር ሲሆን በላይቤሪያና አይቮሪኮስት የእርስ በርስ ጦርነት ጊዜ የሆነውን ከግምት ውስጥ ስናስገባ በአገራችንም ኩላሊት መብላቱና የሰው ልጅን ለጣኦት መስዋእት ማቅረቡ የኩሽ ዘር ነን ለሚሉት የጋራ እምነት መግለጫ ይሆናል የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሰናል። ከዚህ አይነቱ ኋላቀርና ኢሰብአዊ ድርጊት ለመላቀቅ ሰው ሆኖ እንደ ሰው ማሰብን ይጠይቃል፤ከዘመነ ድንጋይ አስተሳሰብ መውጣትን ይጠይቃል።ጎሰኝነትን መቃወምና ማስገድን ይጠይቃል።ከሰፈነው አገር አፍራሽና ሕዝብ አጫራሽ ከሆነው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ሥርዓት መላቀቅን ይጠይቃል።የ21ኛው ክፍለዘመን ትውልድ መሆንን ይጠይቃል።ኢትዮጵያዊ መሆንን ይጠይቃል።

በሚያዝያ 21 ቀን 2015 ዓም በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የመጀመሪያ ቀን የኢሬቻ ጣኦት አከባበር ላይ በጁዋር ሙሃመድ የሚመራ የቄሮ መንጋ ካለምንም ከልካይ ሜዳ ሞልቶ የተለመደውን የአማራ ጥላቻውን ነፍጠኛ ዳውን እያለ ሲጮህ አስተውለናል። አማራ እንዳይገባ በተከለከለበት ከተማው የኦሮሞ አክራሪ ጸረ አማራና ጸረ ኢትዮጵያ ስብስብ በዚህ ደረጃ እንዲንቀሳቀስ የፈቀደው የሥልጣኑ ባለቤት የሆነው ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መንግሥት ነው።ለማጭበርበር ጸረ አብይ አህመድ መፈክር ቢሰማም ዓላማው ሥርዓቱን የሚቃወመውን ሕዝብ የባሰ አደጋ እንደሚጠብቀው በማሳዬት፣ የማስራሪያ መልእክት በመንዛት የባሰ አታምጣ! ብሎ ያለውን ሥርዓት ደጋፊ ሆኖ እንዲኖር፣የኦሮሞ የበላይነትን ተቀብሎ እንዲያድር ለማድረግ ነው።አማራ በመሆኑ ብቻ ሰላማዊ ዜጋ በጥርጣሬ ሲሰቃይ፣ ሲታሠርና ሲታፈን እንደዚህ በአደባባይ ወጥቶ አብይ አህመድንና ሥርዓቱን የሚቃወም የጁዋር ሙሃመድ የጥፋት ሰራዊት እንዴት ተፈቀደለት?የኢትዮጵያ ታሪካዊ ሰንደቅ ዓላማ እዳይያዝ በተከለከለበት ከተማ እንዴት የግብጽ ግልባጭ የሆነው የኦነግ ባንዲራ በነጻ ሊውለበለብ ቻለ?መልሱ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ ነው።የኔ ነው ያሉትን፣የዓላማ አጋራቸውን ይንከባከቡታል እንጂ አይተናኮሉትም።ምናልባትም ተቀያሪ ጎማ አድርጎ የመቀጠል ስልት የመሆኑ ዕድል የሰፋ ነው።ሕዝቡ ለውጥ እያለ ሲጮህ በለውጥ ስም ተቀያሪ የኦሮሙማ ቡድን ሥልጣን ላይ እንዲቀመጥ የማድረግ የውጭና የውስጥ ሃይሎች ጥምረት የፈጠረው ስልት ላለመሆኑ ማረጋገጫ የለም።ያማ ባይሆን ኖሮ ዘመነ ካሴ እስርቤት ሲወረወር ጁዋር ሙሃመድ በቄሮ ሰራዊት ታጅቦ፣የኦነግ ባንዲራ አገልድሞ በኩራት አይኮፈስም ነበር።

የውጭ ሃይሎችም በኤምባሲዎቻቸው በኩል ለመስቀል በዓሉ ያላደረጉትን የመልካም ምኞት መግለጫ ተሽቀዳድመው ለሬቻ በዓሉ ማውጣታቸውን ስንሰማ ጠርጥር ገንፎም አለው ስንጥር ብለን ቀጣዩ እርምጃቸው ምን ሊሆን እንደሚችል ለመከታተል ገፋፍቶናል። እያደር የማናዬው የለም ተከታዩን ለማዬት ያብቃን!

አገራችንንና ሕዝቧን ካለውና ከሚመጣው አደጋ ለማዳን ሁሉም ዘብ ይቁም፤በአንድ ጣራ ሥር ይሰባሰብ።ያንንም እውን የሚያደርግ ሕዝባዊ ድርጅት ይመስረት!

የአዲስ አበባም ሕዝብ ንቃ!ማንቀላፋቱ ይብቃ!!